# ጀግናው ኃይሉ ሻውል

ጀግናው ኃይሉ ሻውል የሰላም አፍቃሪ
የሕዝብ ፍቅር ያለው እውነት ተናጋሪ
ተሰብሰቡ ይላል ለኢትዮጵያ አንድነት
በአንድ ላይ ሆነን እንውጣ ነጻነት::

ጋራ ሽንተረሩን ሜዳና ኮረብታ
ምንም ሳያግደው ጥዋትና ማታ
ከትንሿ ጎጆ ጭስ ብቻ ካላት
ከገጠሬው ጏዳ ከአርሶአደሩ ቤት
ከሕዝቡ ጋር መክሮ ብዙ ተወያይቶ
የበሉትን በልቶ ችግሩንም ሰምቶ
አይዞህ በርታ ብሎ ዞሮ ተዟዙሮ
ከእነርሱም ተምሮ እርሱም አስተምሮ
በመላው ኢትዮጵያ ወገኑን አክብሮ
ለምርጫ አዘጋጅቶ ሁሉም ተወዳድሮ
በ97 ግንቦት ሰባት ዕለት
በምድረ ኢትዮጵያ ታሪክ ታየበት::

ከጨዋታ ውጪ ወያኔን አድርጎት
የዓለም ምስክሮች ሁሉም ባሉበት
ሕዝቡም ድምጹን ሰጠ ለአንድ ቅንጅት
መሪውን መረጠ ያለአንዳች ፍርሃት::

መልኩ ተቀይሮ ድምጽ ተሰረቀ ኮሮጆም ተደፋ
ሕዝብም ወጥቶ ጮኸ በጣምም ተከፋ
ምድር ቀውጢ ሆነች ጊዜው በጣም ከፋ
ወጣቶች ተሰዉ እናቶችም ሞቱ
ጎለማሳው ሲገደል እንዲሁም አዛውንቱ
ማሙሽም ሞተላት ለኢትዮጵያ እናቱ
በአጋዚ ጥይት ከደጁ ከቤቱ::

የስንቱ ቤት ፈርሶ ሌላው አካሉ ጎድሎ
ሌለው ስደት ገባ ውድ አገሩን ጥሎ
ከቤቱ የተያዘው የሕዝብ ተመራጩ እስር ቤት ተጥሎ
ለ20 ወራቶች ስንቱን መከራ አይቶ ካጫንቃው ላይ አዝሎ
ፈገግ ብሎ እያየ ክፉ ሳይናገር ሁሉን አመሳስሎ::

ስንቱን ችሎት ነበር አወይ ጥንካሬ
እውነት እየወጣ እያየነው ዛሬ
ታዲያ እኮ መታሰር ለኃይሉ ምኑ ነው
የእርሱ ጭንቀት ለሕዝብ አብሮት ለታሰረው
መች ረስቶት ያውቃል ወገኑን ላንድ አፍታ
እቆያለሁ አለ ሁሉም ካልተፈታ::

ተፈትቶም ሲወጣ ሕመም ሳይበግረው
የሟቹን ቤተሰብ ሁሉንም ጎበኘው::
የሞቱት ወገኖች ሕያው ነው ስማቸው
ዘላለም ይኖራል ታሪክ ሲያወሳቸው
የሃዘን ዳርቻ ያርግላችሁ በሉ
እግዚአብሔር ያጥናችሁ ወገኖቼ ሁሉ::

የሟችም ቤተሰቦች ስቃዩን አይተው
ለኃይሉ ጤንነት ዓምላክን ተማጽነው
እድሜ እንዲሰጠው ጤናው እንዲሟላ
እነሱም ሊቆሙ ተገንም ሊሆኑ ከፊትና ኋላ::

ኃይሉን ተሽሎታል ሲባል ሰማሁኝ
ሰላም ውሎ አድሯል ይኗዛል ቢሉኝ
ለዓምላክ ምስጋናዬን ቶሎ አቀረብኩኝ::

ኃይሉን ከተሻለው ጤናው ከተሟላ
ተስፋችን ለምልሟል የለም ወደ ኋላ::
የትግሉ መሀንዲስ እርሱ ከተሻለው
ትግላችን ይፋፋም ኃይሉ የእግዚአብሔር ነው::

እርሱ በጣም ብርቱ አይፈራም መከራ
ሁሉን ይቀበላል ከወገኑ ጋራ
ለሕዝብ ለባንዲራው ለሀገር አደራ::

መሪያችን ኃይሉ ነው የሕዝብ ተመራጭ
ልቡ እንደኹ ቆራጥ ነው አይደል ተለዋዋጭ::
ወንዶቹም አስቡ አትሁኑ አድርባይ
እውነትን መስክሩ ውጡ ካደባባይ
ዳግመኛ አቀጣጥሉ የትግል ችቦ አብሩ
ኃይሉን ተከተሉ ሰልፉን አሳምሩ::

ሴቲቱም ተነሺ ምከሪ በጸታሽ
በጠበል በእድሩ በየማህበርሽ
ጌዜው ካለፈብሽ ታሪክ እንዳይወቅስሽ
መቀነትሽ ይጥበቅ ተናገሪ እውነት
መሪያችን ኃይሉ ነው መቆም ነው አንድነት::

መመሪያው አንድነት አብሮ በመሥራት
የሀገር ፍቅር ነው ለኢትዮጵያ እድገት
ኃይላችን ሕዝብ ነው የጠማው ነጻነት::

ወገኖቼ ጽኑ መሪያችን ኃይሉ ነው
የኋላ የኋላ ድሉ የሕዝብ ነው
አይከፋፈልም ቅ ን ጅ ት አንድ ነው::

ማህሌት
ቶሮንቶ ካናዳ
ኖቬምበር 18 ቀነ 2007